MSIE Gotera MCH

# ሾተላይ

MSI ETHIOPIA
REPRODUCTIVE CHOICES

> ሾተላይበመባል የሚታወቀው ክስተት ብዙ ጊዜ አንዷት እናት ከመጀመሪያ እርግዝናዋ በኃላ በተደጋጋሚ የሚከሰት የጽንሱ መጥፋት ነው።

ይህለምን ይሆናል?

የሰዎችደም በአራት መደብ ይከፈላል(A, B, AB, O) እነዚህ ደግሞ እያንዳንዳቸው በሁለት አበይት መደብ ይከፈላሉ፡ አር ኤች ፖዘቲቭ(Rh +) እና አር ኤች ነጌቲቭ(Rh-)።

የሰውየደም ዓይነት ከ እናት እና አባቱ ሚወስደው የደም አይነት ይወሰናል። ከአር ኤች ፖዘቲቭ(Rh +) አባት እና ከአር ኤች ነጌቲቭ(Rh-) እናት የሚፈጠር ጽንስ አር ኤች ፖፖዘቲቭ(Rh +) የመሆን እድሉ የሰፋ ነው።

ሾተላይየሚከሰተው አንዷት ሴት የደም ዓይነቷ አር ኤች ነጌቲቭ (Rh-) ሆኖ አር ኤች ፖዘቲቭ( Rh +) የሆነ ደም ወደ ሰውነቷ ሲገባ ደሟ ውስጥ አር ኤች ፖዘቲቭ(Rh +) የሆኑ የደም ህዋሶችን የሚያጠፋ ንጥረ- ነገር በደሟ ውስጥ ይመረታል። ይህ ንጥረ-ነገር አንዴ ከተመረተ በደሟ ውስጥ እስከ ህይወቷ ፍጻሜ ድረስ ይኖራል።

በማህጸንዋውስጥ የያዘችው ጽንስ የደም ዓይነቱ አር ኤች ፖዘቲቭ ከሆነ የመጀመሪያው ጽንስ ጉዳት አይደርስበትም፣ ነገር ግን የተመረተው ንጥረ-ነገር በቀጣይ እርግዝና ላይ ጽንሱን እንደ ባዕድ አካል ስለሚቆጥረው የ ጽንሱን የደም ሴሎች በማጥቃት ጉዳት ያደርሳል።

በዚህምምክንያት በተደጋጋሚ የምትይዘው ጽንስ የደም ዓይነቱ አር ኤች ፖዘቲቭ ከሆነ እና አስፈላጊው ህክምና ካልተደረገላት ይሞትባታል። የደምዓይነቱ አር ኤች ነጌቲቭ (Rh-) ከሆነ ግን በጤና ይወለዳል። ይህ እንዲሆን ግን የአባትየው የደም ዓይነት አር ኤች ነጌቲቭ (Rh-) መሆን አለበት።

1.ማንኛዋም ሴትከማርገዟ ወይም ማንኛውንም ደም ከመውሰዷ በፊት የደም ዓይነቷን ማወቅ አለባት

2.የወንድ አጋሯንየደም ዓይነት ማወቅ አለባት።

3.እርግዝናው አር ኤችፖዘቲቭ( Rh +) ሆኖ መፈጠሩን እና ንጥረ-ነገሩ አለመመረቱን መጀመሪያ በሚደረግላት ምርመራ (indirect coomb’s test) ማረጋገጥ ይቻላል።

4.ይህ ንጥረ-ነገር እንዳይመረት የሚከላከል መድኃኒት (Anti-D) 7ተኛ ወሯላይ ይሰጣታል።
ከወለደች በኃላ የልጇ የደም ዓይነት አር ኤች ፖዘቲቭ( Rh +) ከሆነ በድጋሚ መድኃኒቱ ይሰጣታል።

5.እርግዝናው ከማህጸን ውጭወይም በውርጃ ቢያበቃም መከላከያውን መድኃኒት መውሰድ ያስፈልጋል።




MSIE Gotera MCH

አድራሻችን:- ወሎሰፈር ወንጌላዊት ህንፃ ፊትለፊት

+251944448060
+251 11 470 0483